
## ምርመራ ማን ማድረግ አለበት?



- በተላላፊ ሳንባ ነቀርሳ (ቲቢ) ከተያዘ ሰው ጋር ግንኙነት የነበረው ሰው።
- በእለታዊ እንቅስቃሴያቸው ፣ አኗኗር፣ ስራ ለሳንባ ነቀርሳ (ቲቢ) ተጋላጭ የሆኑ ሰዎች።

## ምን አይነት ህክምና ያስፈልጋል?

**የሳንባ ነቀርሳ በሽታ ምልክት ካለብዎ**
ሐኪሙ በሽታውን ለመከላከል ሚያስችል መድሃኒት ሊያዝ ይችላል። ሕክምናው በሽታ ለመፈወስ አይደለም፤ ምክንያቱም መደሃኒቱ በታዘዘሎት ወቅት አልታመሙም ። ወደፊት የህመም ምልክቶቹ ወደ ሳንባ ነቀርሳ (ቲቢ) በሽታ እንዳያድግ ለማድረግ ነው። ***ይህ ብዙውን ጊዜ በየቀኑ አንድ ወይም ሁለት መድሀኒቶች ከ3 እስከ 6 ወር መውሰድን ይጠበቅቦታል።***

**የሳንባ ነቀርሳ ህመም መሆኑ ከተረጋገጠ**
ራስን ከበሽታው ማዳን አስፈላጊ ነው። ሕክምናው ረጅም ነው ፣ ቢያንስ ለ6ወራት በየቀኑ በርካታ መድኃኒቶች(አንቲባዮቲክስ) መውሰድ ይጠይቃል። መድሃኒቱን በአግባቡ የወሰዱ እንደሆነ ፥ የመዳን እደልዎ መቶ በመቶ ይሆናል።



## ያነጋግ ሩን : አድራሻ


Fonds des Affections Respiratoires asbl

**ማዕከላዊ ቡድን አድራሻ**
Rue Haute, entrée 290 - 807A
1000 Bruxelles
ስልክ: 02 512 29 36 - Fax : 02 511 14 17
prevention.tuberculose@fares.be

**የብራሰልስ ሳንባ ነቀርሳ መከላከል ማዕከል**
ስልክ: 02 538 05 95
cpt.bruxelles@fares.be

**የሄናውት ሳንባ ነቀርሳ መከላከል ማዕከል**
ስልክ: 071 31 35 04
cpt.hainaut@fares.be

**የሊየጅ ሳንባ ነቀርሳ መከላከል ማዕከል**
ስልክ: 0474 57 16 98 / 0474 57 17 24
cpt.liege@fares.be

**የሉግዘምቡርግ ሳንባ ነቀርሳ መከላከል ማዕከል**
ስልክ: 0474 57 17 28
cpt.luxembourg@fares.be

**የናሙር እና ብራባንት ዋሉን ሳንባ ነቀርሳ መከላከል ማዕከል**
ስልክ: 0474 57 17 10 / 0476 96 28 27
cpt.namur-brabantwallon@fares.be


FARES
Fonds des affections respiratoires asbl


Plus d'infos sur
**www.fares.be**

vivalis .brussels
INAMI
Wallonie Relance
AVIQ


Éditeur responsable : Pr. Van Vooren, FARES asbl. D/2020/5052/1
Illustrations : Christian Papazoglakis – Layout: www.cdcsasbl.be – 11/2024 – Version septembre 2025


AMHARIQUE

# ስለ ሳንባ ነቀርሳ ምን ያውቃሉ?



FARES
Fonds des affections respiratoires asbl

## › የሳንባ ነቀርሳ ምንድን ነው?

የሳንባ ነቀርሳ በሽታ በትንንሽ ህዋሳት (ጀርም) ቲቢ ባሲሊከስ ወይም ኮች ባሲሊከሰ የሚመጣ ነው። የሳንባ ነቀርሳ በዋነኝነት ሳንባን ያጠቃል። እንዲሁም ሌሎች የሰውነት ክፍሎችን እንደ አጥንት፣ አንጀት፣ ኩላሊት እና አእምሮ ያጠቃል።

## › በሳንባ ነቀርሳ ህመም ማን ሊጠቃ ይችላል?


ሳንባ ነቀርሳ ተላላፊ በሽታ ነው ።



የሳንባ ነቀርሳ (ቲቢ) ባሲለሶች በሳንባ ነቀርሳ በተጠቃ ሰው ሳንባ ውስጥ ይገኛሉ ። በበሽታው የተያዘ ሰው ሲያስል ፣ ሲያስነጥስ ወይም ሲናገር ጀርሞቹ አየር ላይ ይርቃሉ ። አንድ ሌላ ሰው ይህን አየር ወደ ውስጥ ቢስብ ጀርሞቹ በተመሳሳይ ጊዜ ይለቀቃሉ ።

ማንም ሰው በሳንባ ነቀርሳ አስተላላፊ ተህዋሳት (ቲቢ ባሲሊከስ) ሊለከፍ (ሊያዝ) ይችላል። ይሁን እንጂ አንዳንድ ሰዎች ከሌሎች ይበልጥ በበሽታው የመያዝ እድላቸው ከፍተኛ ነው ። እንደ አኗኗር ሁኔታ እና እንደ ሥራ አይነት በሳንባ ነቀርሳ በሽታ ከተያዙ ሰዎች ጋር አዘውትረው የሚገናኙ ከሆነ በበሽታው የመያዝ እድልዎ ከፍተኛ ነው ።

## › በድብቅ የሳንባ ነቀርሳ እና በንቁ የሳንባ ነቀርሳ ማካከል ያለ ልዩነት ምንድን ነው?



በሚተነፍሱበት ወቅት የሳንባ ነቀርሳ አምጪ ተህዋሳት (ቲቢ ባሲላይ) ወደ ሳንባ ዘልቀው ይገባሉ። በሰውነት ውስጥ ያለው መከላከያ አቅም፥ ህመም አምጪ ተህዋሳት ላይ ጥቃት የሚሰነዝሩ ሲሆን አብዛኛውን ጊዜ እነዚህን ተህዋሳት ያስወግዳል ። ተህዋሳቱ በሰውነት ውስጥ ከቀሩ አብዛኛውን ጊዜ ንቁ አይደሉም ወይም ጀርሞቹ ህይወት ቢኖራቸውም "ተኝተዋል"።ይህም ማለት አደገኛ አይደሉም ።የ ድብቅ ድብቅ ነቀርሳ በሽታ ካለብዎ ፤ ግን የህመም ምልክት ከሌለብዎ ፤ ለሌላ ሰው አያስተላልፉም።

በእድሜ የገፉ ከሆነ ፣ ወይም ልጅ ከሆኑ አልያም በሌሎች በሽታዎች የተዳከሙ ከሆነ ፣ በሰውነትዎ ውስጥ ያለው የመከላከያ አቅም ጀርሞችን (ተህዋሳትን) ለመዋጋት ደካማ ሊሆን ይችላል። እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ካጋጠመ "የተኙት" ሳንባ ነቀርሳ ተህዋሳት ሊነቃቁ ፣ ሊባዙና የንቁ ሳንባ ነቀርሳ በሽታ ሊያስከትሉ ይችላሉ ።

ሳንባን የሚያጠቃ የንቁ ሳንባ ነቀርሳ በሽታ ካለብዎ የሚከተሉትን ምልክቶች ሊያዩ ይችላሉ፥

- ሳል
- አክታ ያለው ሳል (አንዳንድ ጊዜ ደም የተቀላቀለበት)
- ድካም
- ትኩሳት
- ሌሊት ላብ
- ክብደት መቀነስ

**ከእነዚህ ምልክቶች መካከል አንዱ የሚሰቃዩ ከሆነ በተቻለ ፍጥነት ሐኪም ዘንድ ይሂዱ!**

## › በሳንባ ነቀርሳ በሽታ በተያዘ ሰው የተጋለጡ ሰዎች፥ በበሽታው መያዛቸውን ወይም አለመያዛቸውን እንዴት ማወቅ ይቻላል?

ሐኪም በሳንባ ነቀርሳ ህማም አምጪ ተህዋሰ መያዙን ወይም አለመያዙን ለማወቅ የሚያስችል ቱበርክሊን የተባለ በመርፌ የሚሰጥ ህክምና ያደርጋል። የህክምና ውጤት ከ3-5 ባሉት ቀናት ይደርሳል። ምርምራው ቱበርክሊን የቆዳ ምርመራ በመባል ይታወቃል ወይም በቀድሞ አጠራር ኢንትራደርማል ሪአክሽን ወይም ማንቶክስ ምርመራ በመባል ይታወቃል። የምርመራ ውጤቱ በጤና ባለሞያ መተርጎም (መገለጽ) አለበት።

ምርመራው ፖዘቲቭ (አዎንታዊ) ከሆነ የደረት ራጅ መነሳት አለበት:-

- › የራጅ ውጤት የተለየ ነገር የማያሳይ ከሆነ የድብቅ ሳንባ ነቀርሳ አለብዎ ማለት ነው ።
- › አለዚያ የ ንቁ ሳንባ ነቀርሳ መኖሩን ለማወቅ ተጨማሪ ምርመራዎች ያስፈልጋሉ ለምሳሌ:- ምራቅ ውስጥ ተላላፊ የሳንባ ነቀርሳ ህማም አምጪ ተህዋሳት መኖሩን መመርመር።



ሳል




አክታ የተቀላቀለበት ሳል




ድካም



ትኩሳት



ሌሊት ላብ



ክብደት መቀነስ